የሰ/መ/ቁ. 64845

የካቲት 26 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ሐጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- አቶ ሀብቱ ሀጋዚ - ቀረቡ

ተጠሪዎች፡- 1- የኮምቦልቻ ግብርና ሙያ ማሰልጠኛ ኮሌጅ - አበበ ዘውዱ ቀረቡ

2- አቶ ዑመር የሱፍ - አልቀረቡም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የአንደኛ ተጠሪ ንብረት የሆነችውን ኮድ 4-00242 የሆነች መኪና በሁለተኛው ተጠሪ በመሽከርከር ላይ እያለ የአካል ጉዳት የደረሰበት መሆኑን ገልፆ ያቀረበውን የካሣ ጥያቄ በመቀበል ፣ ለደረሰው ጉዳት ሙሉ በሙሉ ኃላፊዎች ተጠሪዎች ናቸው፡፡ ተጠሪዎች ለአመልካች ብር 63,000 /ስልሣ ሶስት ሺህ ብር/ ካሣና ለህክምና የወጣውን ብር 11,277.90/አሥራ አንድ ሺህ ሁለት መቶ ሰባ ሰባት ብር ከዘጠና ሣንቲም/ ይክፈሉ በማለት የሐረሪ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 05073 ሰኔ 29 ቀን 2002 ዓ.ም በሰጠው ውሣኔ አንደኛ ተጠሪ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለሐረሪ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርቧል፡፡ የሐረሪ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት አንደኛ ተጠሪና አመልካች ያቀረቡትን ክርክር ከሰማ በኋላ ለደረሰው ጉዳት አመልካች በከፊል ኃላፊነት አለበት በማለት አንደኛ ተጠሪ አመልካች ለህክምና ወጭ ያደረገውን ብር 11,277.90 /አሥራ አንድ ሺህ ሁለት መቶ ሰባ ሰባት ብር ከዘጠና ሣንቲም/ ብቻ ይክፈል በማለት በመዝገብ ቁጥር 01663 ጥቅምት 30 ቀን 2003 ዓ.ም የሰጠውን ውሣኔ በሰበር ታይቶ እንዲታረም ነው፡፡

አመልካች ጥር 23 ቀን 2003 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ የሐረሪ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ የሐረሪ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በከፊል በመሻር የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት መሆኑን በመዘርዘር አመልክተዋል፡፡ ጉዳዩ በሰበር የሚጣራ ነጥብ ያለው መሆኑ ተገልፆ ጭብጥ ተመርቶ ተጠሪ መልስ እንዲሰጥበት መጥሪያ በመላኩ ተጠሪ መልስ ሰጥቷል፡፡ አመልካች በፅሑፍ የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

እኛም በመጀመሪያ በሰበር የተያዘውን ጭብጥ ከመወሰናችን በፊት ጉዳዩ የይግባኝ ደረጃውን የጨረሰና በሰበር ለመታየት የሚችል ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ ማየቱ አስፈላጊ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ጉዳዩን እንደመረመርነው በሐረሪ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የተከራከሩት ተከራካሪ ወገኖች የሁለት ክልል ኗሪዎች ናቸው፡፡ አመልካች የሐረሪ ክልል ነዋሪ ሲሆን ተጠሪ የኦሮሚያ ክልል የተቋቋመ የግብርና ሙያ ማሰልጠኛ ኮሌጅ ነው፡፡ ይህም በመሆኑ የሐረሪ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ጉዳዩን በመቀበል አከራክሮ የወሰነው በህገ መንግስቱ አንቀፅ 80 ንዑስ አንቀፅ 4 በተሰጠው

የፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት የውክልና ሥልጣኑ ነው፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ጉዳዩን በይግባኝ በማየት የወሰነው በህገመንግስቱ አንቀፅ 80 ንዑስ አንቀፅ 2 በተሰጠው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የውክልና ሥልጣን ነው፡፡

ጉዳዩ በአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀፅ 5 ንዑስ አንቀፅ 2 መሠረት የፌደራል ጉዳይ ከሆነና የሐረሪ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የውክልና ሥልጣኑ አይቶ የሰጠውን ውሣኔ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በውክልና በተሰጠው ሥልጣን አይቶ ከለወጠው አመልካች ይግባኝ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ማቅረብ እንዳለበት አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀፅ 9 ንዑስ አንቀፅ 2 በግልፅ ይደነግጋል፡፡ አመልካች የሰበር አቤቱታ ያቀረበው በመጀመሪያ ውሣኔው በይግባኝ እንዲታይለት ለፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ጉዳዩን ሣያቀርብና ይግባኝ ሰሚው ችሎት የመጨረሻ ውሣኔ ሣይሰጥበት ነው፡፡ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት በዳኝነት አይቶ ውሣኔ የሚሰጠው በይግባኝ ታይተው የመጨረሻ ውሣኔ ባገኙ ጉዳዮች ላይ እንደሆነ በህገ መንግስቱ አንቀፅ 80 ንዑስ አንቀፅ 3/ሀ/ ተደንግጓል፡፡

ስለሆነም አመልካች የይግባኝ ደረጃውን ሣይጨርስ ጉዳዩ በሰበር ታይቶ እንዲወሰንለት ያቀረበው አቤቱታ የህግ መሠረት የሌለው በመሆኑ አልተቀበልነውም፡፡

**<u>ው ሣ ኔ</u>**

አመልካች ይግባኝ ለፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በማቅረብ ጉዳዩ የመጨረሻ ውሣኔ እንዲያገኝ ሣያመለክት በሰበር ችሎት ያቀረበውን አቤቱታ ለማስተናገድ የሚችልበት የህግ መሠረት የሌለ በመሆኑ አልተቀበልነውም፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሃ/ዲ